# የመንግሥት ብድር አስተዳደር እና ዋስትና አሰጣጥ መመሪያ

# ቁጥር 46/2009

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር

ጥር 2009 ዓ.ም

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አውጪው ባለሥልጣን**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ 75 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

2. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የመንግሥት ብድር አስተዳደር እና ዋስትና አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 46/2009" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

3. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ ያሉ ቃላትና ሃረጎች በመንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 እና በፋይናንስ ደንብ ቁጥር 190/2002 የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡ከዚህም በተጨማሪ በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. "የመንግሥት ብድር" ማለት የፌዴራል መንግሥት በባለሁለት ወገን ወይም በባለብዙ ወገን ስምምነት መሠረት ከአገር ውስጥም ሆነ ከውጭ አገር ምንጭ በብድር የሚያገኘው ገንዘብ ነው፡፡

2. "የውጭ ብድር ፍሰት" ማለት በብድር ስምምነት መሠረት ወደ አገር ውስጥ የገባ የገንዘብ ወይም የሀብት መጠን እና በቀጥታ ለሥራ ተቋራጭ ወይም ለአማካሪ የተከፈለ ክፍያ ነው፡፡

3. "የግምጃ ቤት ሰነድ" ማለት ለበጀት ጉድለት መሸፈኛ የሚውል ገንዘብ ለማሰባሰብ ለገበያ የዋለ የብድር ሰነድ ነው፡፡

4. "የመልሶ ማበደር ስምምነት" ማለት በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴርና የብድሩ ተጠቃሚ በሚሆነው ድርጅት መካከል የሚፈረም በብድር የተገኘን ገንዘብ መልሶ ለማበደር የሚያስችል የስምምነት ሰነድ ነው፡፡

5. "የብድር ስትራቴጂ" ማለት በየ5 ዓመቱ የሚዘጋጅና በየዓመቱ የፊሲካልና የማክሮ ኢኮኖሚ መረጃዎችን መሠረት በማድረግ የሚከለስ የመንግሥት የብድር አስተዳደር ስትራቴጂ የሚገለጽበት ሰነድ ነው፡፡

6. "የዕዳ ጫና ትንተና" ማለት ለተለያዩ የልማት ዕቅዶች ማስፈጸሚያ የተወሰዱ ብድሮች ያሉበትን ሁኔታ፣ ወደፊት የሚወሰዱ ብድሮች በማክሮ ኢኮኖሚው ላይ ያላቸውን አወንታዊና አሉታዊ ተጽዕኖ አገሪቱ ካላት ዕዳን የመሸከምና የመክፈል አቅም ጋር በማነጻጸር የሚሰራ ትንተና ነው፡፡

7. "የመንግሥት ብድር አማካሪ ኮሚቴ" ማለት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 15 መሠረት የሚቋቋም ኮሚቴ ነው፡፡

8. "የማህበራዊ ፕሮጀክት" ማለት መንግሥት ለኅብረተሰቡ በነፃ ከሚያቀርባቸው የሕዝብ አገልግሎቶች ጋር የተያያዘ ፕሮጀክት ሲሆን፣ የትምህርት፣ የጤና፣ የመጠጥ ውሃ እና የመንገድ ፕሮጀክቶችን ይጨምራል፡፡

9. "የመንግሥት የልማት ድርጅት" ማለት በአዋጅ ቁጥር 25/1984 መሠረት የተቋቋመ ድርጅት ነው፡፡

10. "ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር" ማለት እንደአግባብነቱ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፡፡

## 4. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ተብለው በተመለከቱት እንዲሁም ከውጭ አገር ምንጮች ገንዘብ የመበደር ሥልጣን በተሰጣቸው የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ላይ ሁሉ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 5. <u>የመመሪያው ዓላማ</u>

የዚህ መመሪያ ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

1. ለዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት የሚያግዝ የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ዕድገት እንዲኖር ለማድረግ፣

2. በአዋጅ ቁጥር 648/2001 (እንደተሻሻለው) እና በአንዳንድ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንቦች ለሚኒስቴሩ ከተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት አንጻር የብድር ውል ስምምነት በተገቢው መንገድ እንዲፈጸም ለማድረግ፣

3. በብድር ውሉ መሠረት ወደ አገር ውስጥ የሚፈሰው የገንዘብ መጠን በወቅቱ እንዲገባና ለሥራ ተቋራጮችና ለአማካሪዎች በቀጥታ ክፍያ የተፈፀመው ገንዘብ በትክክል በአገሪቱ የብድር መረጃ ቋት ውስጥ እንዲመዘገብ ክትትል ለማድረግ፣

4. የአገር ውስጥ እና የውጭ አገር ብድር አወሳሰድ በትክክል እንዲመራ ለማድረግ፣

5. የውጭ አገር እና የአገር ውስጥ ብድር በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን እና በብድር ስምምነቱ መሠረት ተመልሶ መከፈሉን ለመቆጣጠርና ለመከታተል፣

6. አስፈጻሚ መሥሪያ ቤቶች በውጭ ብድር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶችን ከዝግጅት ጀምሮ እስከሚጠናቀቁ ድረስ በተዘጋጀው መመሪያ መሠረት እንዲያከናውኑ ለማድረግ፣

7. ከውጭ የሚገኙ ብድሮች አገሪቷ የምታካሂደውን የልማት እንቅስቃሴ በተሻለ ሁኔታ እንዲደግፉና ተጨባጭ ውጤት እንዲያመጡ ወጥ የሆነ የአሰራር ሥርዓት ለመዘርጋት፣

## ክፍል ሁለት

## ብድርና ዋስትና

### 6. የዕቅድና ስትራቴጂ መጣጣም

የመካከለኛ ዘመን ብድር ስትራቴጂ እና የዕዳ ጫና ትንተና ከማክሮ ኢኮኖሚና ፊስካል ማዕቀፍ እንዲሁም ከአገሪቱ የረጅምና የአጭር ጊዜ የልማት ዕቅድ ጋር መጣጣም አለባቸው፡፡

## 7. የአገር ውስጥ ብድር

1. ሚኒስቴሩ፡-

ሀ/ የበጀት ጉድለትን ለመሸፈን የሚወሰደው ብድር ከማክሮ ኢኮኖሚና ፊስካል ማዕቀፍ እንዲሁም ከገንዘብ ፖሊሲ ጋር የተጣጣመ መሆኑን በማረጋገጥ ይበደራል፡፡

ለ/ ለበጀት ጉድለት ማሟያ እንዲውል ለገበያ የሚቀርበውን አዲስ የግምጃ ቤት ሰነድ መጠን ለይቶ ያቀርባል፣ ዓይነቱንም ይወስናል፡፡

ሐ/ የግምጃ ቤት ሰነድ ሽያጭን ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ጋር በመተባበር ያከናውናል፡፡

2. ሚኒስቴሩ የበጀት ጉድለትን ለመሸፈን የሚወስደው ብድር የግምጃ ቤት ሰነድ በመሸጥ ወይም በቀጥታ ብድር ሊሆን ይችላል፡፡

3. የመንግሥት ቦንድ እና ልዩ ቦንድ ለገበያ የሚቀርበው በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሲፈቀድ ብቻ ይሆናል፡፡

## 8. የውጭ ብድር

1. ሚኒስቴሩ ዓመታዊ እና የመካከለኛ ዘመን የውጭ ብድር ፍላጎትና የብድር ክፍያዎችን ዕቅድ በማዘጋጀት በፊስካል ማዕቀፍ ውስጥ ማካተት ይኖርበታል፡፡

2. የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የውጭ ብድር ጥያቄዎቻቸውን ቅደም ተከተል በማስያዝ፣ የመንግሥትን ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ፕሮግራሞች መሠረት በማድረግ ለሚኒስቴሩ ማቅረብ አለባቸው፡፡

3. የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ከውጭ አገር ምንጮች ብድር ለመውሰድ ከሚያቀርቡት ጥያቄ ጋር የፕሮጀክቱን የአዋጭነት ጥናት እንዲሁም በብድር የሚወስዱትን ገንዘብ ለመክፈል የሚያስችል የፋይናንስ አቅም ያላቸው መሆኑን የሚያሳይ ጥናት አያይዘው ማቅረብ አለባቸው፡፡

4. ሚኒስቴሩ የቀረበውን የውጭ ብድር ጥያቄ በመገምገም ከብድር ስትራቴጂው ጋር የሚጣጣም ሆኖ ካገኘው የፋይናንስ ጥያቄውን ለአበዳሪ አገሮችና ፋይናንስ ተቋማት ያቀርባል፣ የድርድር ሥራዎችን ይመራል፣ የሚመለከታቸው የሥራ

ክፍሎችና አስፈጻሚ መሥሪያ ቤቶች በድርድሩ ከጅምር እስከ ፍጻሜ እንዲሳተፉ ያደርጋል፣

5. መንግሥት ለልማት ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ የሚውል ብድር ከውጭ አገር መንግሥታትና ከአለም አቀፍ ፋይናንስ ተቋማት ጫናው ቀላል የሆነ (Concessional) ወይም የንግድ ብድር ሊወስድ ይችላል። ሆኖም በሚኒስትሩ በሚሰጥ ልዩ ውሳኔ ካልሆነ በስተቀር ለማህበራዊ ፕሮጀክቶች የንግድ ብድር መውሰድ አይቻልም።

6. መንግሥት በየዓመቱ ለሁሉም የብድር ዓይነቶች ከሚቀመጠው አጠቃላይ የብድር ጣሪያ በላይ መበደር አይችልም። ጣሪያው ሚኒስቴሩ በሚያዘጋጀው የብድር ጫና ትንተና መሠረት ይወሰናል።

7. ማንኛውም ብድር ከመወሰዱ በፊት አዲስ የሚወሰደው ብድር በመንግሥት ጫናው ቀላል የሆነ እና የንግድ ብድር መጠን መካከል ሊኖር የሚገባውን ስብጥር የማያዛባ መሆኑ መረጋገጥ አለበት። ይህም ስብጥር በብድር ስትራቴጂው ውስጥ መመልከት ይኖርበታል።

8. ሚኒስቴሩ በተቻለ መጠን ጫናው ቀላል የሆነ ብድር የሚገኝበትን መንገድ ማመቻቸት ይኖርበታል። ሆኖም ሌላ የብድር አማራጭ ከታጣ ጫናው ቀላል ላልሆነ ብድር የተቀመጠውን የብድር ጣሪያ ሳያልፍ ብድር መውሰድ ይችላል።

9. ሚኒስቴሩ ለፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ የሚወሰድ ብድር በሀብት ግንባታ ላይ የሚውል መሆኑን ማረጋገጥ አለበት። ስለሆነም ከብድሩ ገንዘብ ላይ ለጥናት፣ ለአማካሪዎች ቅጥር፣ ለሥልጠና (ከፕሮጀክት ጋር በቀጥታ ለሚያያዙ ሥልጠናዎች ብቻ) እና ለአስተዳደራዊ ጉዳዮች የሚመደቡ ወጪዎች መጠን ዝቅተኛ መሆን ያለበት ሲሆን፣ ከፕሮጀክቱ አጠቃላይ ወጪ 10 በመቶ መብለጥ የለበትም።

10. የፕሮጀክት አስተዳደራዊ ወጪዎች ለብድሩ ፕሮጀክት አፈጻጸም አስፈላጊ ሆነው ሲገኙ በመንግሥት አቅም የሚሸፈኑበት ሁኔታ በቅድሚያ መታየት አለበት።

11. ሚኒስቴሩ በውጭ ገበያ የሚሸጥ ቦንድ መጠንና ዓይነት በብድር ስትራቴጂው መሠረት መሆኑን ያረጋግጣል፣ በሕዝብ በተወካዮች ምክር ቤትም እንዲጸድቅ ያደርጋል።

12. የውጭ አገር ብድር ወጪ በሚሠላበት ጊዜ ከወለድ በተጨማሪ ለኢንሹራንስ አረቦን እና ከብድሩ ጋር የተያያዙ ሌሎች ክፍያዎችን አካቶ ጠቅላላው ወጪ በትክክል መሠላት ይኖርበታል።

## 8. <u>የብድር ዋስትና</u>

1. ከሚኒስቴር መ/ቤቱ በስተቀር ማናቸውም ሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ለሦስተኛ ወገኖች ግዴታ መፈፀም ዋስትና መስጠት አይችልም።

2. ሚኒስቴሩ ለብድር መክፈል ዋስትና ሊሰጥ የሚችለው ብድሩ ሙሉ በሙሉ በመንግሥት ባለቤትነት የሚካሄዱ የልማት ድርጅቶች ለሚያከናውኑትና በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በፀደቀው ዕቅድ ውስጥ ለተካተቱ ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ የሚውል ከሆነ ብቻ ነው።

3. የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ከውጭ አገር በሚገኝ ብድር የሚያከናውኑትን ፕሮጀክት የግንባታ ውል ከሥራ ተቋራጮች ጋር ከመፈረማቸው በፊት የብድሩ የውል ቃሎችና ሁኔታዎች ተቀባይነት ያላቸው መሆኑን ወይም የመንግሥት ዋስትና ሊሰጥ የሚችል መሆኑን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ ከሚኒስቴሩ ማግኘት አለባቸው።

4. ሚኒስቴሩ የብድር ዋስትናን በደብዳቤ ወይም የዋናውን ባለዕዳ ግዴታ የሚጠጣ መሆኑን የሚያሳይ ማረጋገጫ በማናቸውም መልክ ሊሰጥ ይችላል።

5. የሚዘጋጀው የብድር ዋስትና ሰነድ ከመሰጠቱ በፊት የመሥሪያ ቤቱ የሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች አስተያየት እንዲሰጡበት መደረግ ይኖርበታል።

6. ሚኒስቴሩ የብድር ዋስትና ከመስጠቱ በፊት የፕሮጀክቱ አዋጭነት በሚመለከተው አካል መታየቱን ያረጋግጣል፣ የመሥሪያ ቤቱ የተመረመረ የኦዲት ሪፖርት እንዲቀርብ ያደርጋል፣ የብድሩን ዓይነትና የፕሮጀክቱን አግባብነት/ትስስር በሚገባ ማየት ይኖርበታል።

7. ዋስትና መስጠት አስፈላጊና ተገቢ መሆኑን ሲያምንበት የብድር ዋስትናው የሚሰጥባቸውን የውል ቃሎችና ሁኔታዎች ይወስናል።

# ክፍል ሦስት

## የጥሪት ፈንድ እና መልሶ ማበደር

### 9. የጥሪት ፈንድ

1. የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች አዲስ የጥሪት ፈንድ ለማቋቋም ያላቸውን ሀሳብ በቅድሚያ ለሚኒስቴሩ መላክ አለባቸው፡፡

2. በሕግ በተለየ ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር፣ ማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ከሚኒስትሮች ምክር ቤት ፈቃድ ሳያገኝ የጥሪት ፈንድ ማቋቋም አይችልም፡፡

### 10. መልሶ ማበደር

1. ከውጭ አገር በብድር የተገኘው ገንዘብ ተጠቃሚ የመንግሥት የልማት ድርጅት ወይም ከፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ውጪ የሆነ መሥሪያ ቤት ሲሆን፣ የመልሶ ማበደር ስምምነት በሚኒስቴሩ እና በብድሩ ተጠቃሚ መካከል እንዲፈረም ይደረጋል፡፡

2. የመልሶ ማበደር ስምምነት ተበዳሪዎች በመልሶ ማበደር ስምምነት የተበደሩትን ገንዘብ በስምምነቱ መሠረት ወደተጠቃለለው ፈንድ በወቅቱ ገቢ ማድረግ አለባቸው፡፡

3. የመልሶ ማበደር ስምምነት በብድር የተሰጠውን የገንዘብ መጠን፣ የወለድ መጠን፣ የአገልግሎት ክፍያዎች፣ የብድሩ ገንዘብ በስምምነቱ በተመለከተው ጊዜ ባይከፈል የሚጣለውን የቅጣት ወለድ፣ የችሮታ ጊዜ፣ የዋና ብድር ክፍያ የሚጀምርበትና ብድሩ ተከፍሎ የሚያልቅበት ጊዜ እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ የተባሉ ጉዳዮችን መያዝ አለበት፡፡

4. ሚኒስቴሩ በመልሶ ማበደር ስምምነት የተላላፈን ብድር የመክፈያ ጊዜ መዝግቦ በመያዝ በስምምነቱ በተገለጸው ጊዜና መጠን ብድሩ መመለሱን ይከታተላል፡፡

5. ሚኒስቴሩ ለፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የተገኘን ብድር ለአስፈጻሚ መሥሪያ ቤቶች ወይም የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በመልሶ ማበደር ስምምነት

ከማስተላለፉ በፊት የሚመለከታቸው የሚኒስቴሩ መሥሪያ ቤት የሥራ ክፍሎች በመልሶ ማበደር ስምምነቱ ረቂቅ ላይ አስተያየት እንዲሰጡበት ይደረጋል፡፡

6. በአበዳሪዎች የሚወሰን የወለድ መጠን በሌለበት ሁኔታ ሚኒስትሩ በመልሶ ማበደር ስምምነት ባስተላለፈው ገንዘብ ላይ የሚከፈለውን የወለድ መጠን ሊወስን ይችላል፡፡

## 11. በብድር የተገኘን ገንዘብ ለተጠቃሚው ማስተላለፍ

1. በብድር ስምምነቱ ተለይቶ የተመለከተ ከሆነ በሚኒስቴሩና የፕሮጀክቱ አስፈጻሚ በሆነው የመንግሥት መሥሪያ ቤት መካከል የብድሩን ገንዘብ አጠቃቀም የሚወሰን የማስተላለፊያ ስምምነት ሊፈረም ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚተላለፈው ገንዘብ ተመልሶ የሚከፈል ወይም በመልሶ ማበደር የሚመዘገብ አይሆንም፡፡

# ክፍል አራት

## የዕዳ ጫና ትንተና፣ የመካከለኛ ዘመን ብድር ስትራቴጂ እና የብድር ሂሳብ ሪፖርት አቀራረብ

## 12. የዕዳ ጫና ትንተና

ሚኒስቴሩ የአገሪቷን የብድር አወሳሰድ በዕቅድ ለመምራት የሚያስችል የክፍያ ሚዛንን እና የገንዘብ ፖሊሲን መሠረት ያደረገ እንዲሁም የመክፈል አቅምን ከግምት ውስጥ ያስገባ የዕዳ ጫና ትንተና ማዘጋጀት አለበት፡፡

## 13. የመካከለኛ ዘመን የብድር ስትራቴጂ

ሚኒስቴሩ፡-

1. የመካከለኛ ዘመን ብድር ስትራቴጂ ያዘጋጃል፣ ይህም ስትራቴጂ በየዓመቱ እንዲከለስ ያደርጋል፡፡

2. ለተለያዩ የልማት ዕቅዶች ማስፈጸሚያ የሚያስፈልገው ተጨማሪ የብድር ሀብት ከመካከለኛ ዘመን የብድር ስትራቴጂ ጋር የሚጣጣም መሆኑን ያረጋግጣል፣ የብድሩን ሂደት በዋናነት ያስተባብራል።

## 14. የብድር ሂሳብ ሪፖርት አቀራረብ

1. የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከሚያስፈጽሙት ፕሮጀክት ጋር በተያያዘ የብድር ፍሰት የአጠቃቀም ሪፖርቱን በየወሩ ወሩን በገባ በ5 ቀናት ውስጥ፣ የመንግሥት ልማት ድርጅቶች የሶስት ወሩ ሪፖርት ሩብ ዓመቱ በተጠናቀቀ በ10 ቀናት ውስጥ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በተዘጋጀው ቅጽ መሠረት ማቅረብ አለባቸው።

2. በተቋቋሙበት ሕግ ከውጭ አገር ምንጮች የመበደር ሥልጣን የተሰጣቸው የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ከውጭ አገር ከተለያዩ ፋይናንስ ተቋማት የተበደሩትን ገንዘብ መጠን፣ ከአበዳሪው የተላከላቸውን የብድር ገንዘብ ፍሰት፣ በተበዳሪዎች የሚፈጸሙ የወለድና የዋና ክፍያዎች ሪፖርት ሚኒስቴሩ ባዘጋጀው ፎርማት መሠረት ወይም በኤሌክትሮኒክስ የመረጃ ሥርዓት ዘዴ በመጠቀም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተገለፀው ጊዜ ውስጥ ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

3. የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ከአገር ውስጥ ባንኮች የሚወስዱትን የረጅም ጊዜ ብድር መጠን የሚያሳይ ሪፖርት በየሩብ ዓመቱ ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ሩብ ዓመቱ በተጠናቀቀ በ10 ቀናት ውስጥ ማቅረብ አለባቸው።

4. ሚኒስቴሩ የብድር ሂሳብን በዋናው ኦዲተር መ/ቤት የማስመርመርና ተገቢውን ማብራሪያ የመስጠት ኃላፊነት አለበት።

# ክፍል አምስት

# የመንግሥት ብድር አማካሪ ኮሚቴ

## 15. የመንግሥት ብድር አማካሪ ኮሚቴ ስለማቋቋም

የኢትዮጵያ መንግሥት እና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ከውጭ አገር የሚወስዱትን ብድር አፈጻጸም የሚከታተል የመንግሥት የብድር አማካሪ ኮሚቴ ከዚህ በኋላ "ኮሚቴ" ተብሎ የሚጠራ በዚህ መመሪያ ተቋቁሟል።

## 16. የኮሚቴው አባላት

ኮሚቴው የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

1. የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ወይም እርሱ የሚወክለው ........................................................... ሰብሳቢ
2. የብድር አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ......................... ፀሐፊ
3. የሕግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር .......................... አባል
4. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ተወካይ ...................................... አባል
5. የትሬዠሪ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ...................................... አባል
6. የመንግስታት ትብብር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ..................... አባል
7. የዓለም አቀፍ ፋይናንስ ተቋማት ትብብር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር.. አባል
8. የፊስካል ፖሊሲ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ............................. አባል
9. የኢትዮ ቻይና የልማት ትብብር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር .......... አባል
10. የበጀት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ................................................ አባል
11. ሚኒስትሩ ሊሳተፉ ይገባቸዋል የሚላቸው ተሳታፊዎች ................ አባል

## 17. የኮሚቴው ተግባርና ኃላፊነት

1. ኮሚቴው የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፣

   ሀ/ የብድር አስተዳደር ስትራቴጂ ከአገሪቱ ሕግና ከሌሎች የመንግሥት ፖሊሲዎች ጋር መጣጣሙን ማረጋገጥ፣

ለ/ ማናቸውም የውጪ አገር ብድር የሚያስከትላቸውን ወጪዎች ሁሉ በስሌት ውስጥ የሚያስገባ የብድሩ የወጪ ጫና የሚሠላበት ማንዋል ማዘጋጀት፣

ሐ/ ዓመታዊ የወጪ አሸፋፈን ዕቅድ እንዲጸድቅ እና ፕሮጀክቶችን በውጭ ፋይናንስ ለማከናወን በተቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎች ላይ ሀሳብ የማቅረብ፣

መ/ የብድር ትንተናን ከግምት ውስጥ በማስገባት የብድሩ መወሰድ በመንግሥት ዕዳ ክምችት ላይ የሚኖረውን ውጤት መገምገም፣

ሠ/ ጫናው ቀላል ያልሆነ ብድር በሚሆንበት ጊዜ የግንባታ ሥራ ውል ከመፈረሙ በፊት የወጪ አሸፋፈንን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ የቀረቡትን አስተያየቶች አይቶ ሀሳብ ማቅረብ፣

ረ/ ከፋይናንስ ተቋማት ጋር በብድሩ የውል ቃሎችና ሁኔታዎች (Terms and Conditions) ላይ ድርድር እንዲካሄድና የድርድር ቡድን እንዲሰየም ሀሳብ ማቅረብ፣

ሰ/ ከፋይናንስ ተቋማት የቀረቡ የውል ቃሎችና ሁኔታዎችን በመገምገም ለሚኒስትሩ ድርድሩ ስለሚመራበት አኳኋን የውሳኔ ሀሳብ ማቅረብ፣

ሸ/ በብድር ስምምነቱ ላይ በተደረገው ድርድር የተገኘውን ውጤት በመገምገም ለሚኒስትሩ ሀሳብ ማቅረብ፣

2. ኮሚቴው የራሱን የአሰራር ደንብ ያወጣል፡፡

3. ከዚህ በላይ የተደነገገው ቢኖርም ጫናው ቀላል የሆነ ብድር በሚሆንበት ጊዜ ጉዳዩ ለብድር አማካሪ ኮሚቴ ቀርቦ እንዲታይ ማድረግ ሳያስፈልግ ሚኒስትሩ ከሚመለከታቸው አካላት (ጉዳዩን በባለቤትነት ከሚመራው ዳይሬክቶሬት ከብድር አስተዳደር ዳይሬክቶሬት እና ከሕግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት) በሚቀርብለት አስተያየት መሠረት ውሣኔ ለመስጠት ይችላል፡፡

## 18. <u>የተሻሩ መመሪያዎች</u>

የመንግሥት ዕዳ አስተዳደርና ኢንቨስትመንት መመሪያ ቁጥር 3/1991 ተሽሮ በዚህ መመሪያ ተተክቷል፡፡

## 19. የመመሪያው ተፈጻሚነት

ይህ መመሪያ ከ የካቲት 01 ቀን 2009 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥር 24 ቀን 2009

አብራሃም ተከስተ (ዶ/ር)
የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር
ሚኒስትር